*የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን*
ምርጫው በኀቸው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# *እስከመቼ*

ጥር ፳፫ እስከ ጥር ፳፱ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
January 31 to February 6, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፪
Volume I Number 2

# ልዩ ዕትም

## *ወቅታዊ የፖለቲካ አሠላለፋችንን በቀጥታ በመመልከት መፍትሄ ጠቋሚ*

## ኅብረት ለትግል ለኅብረት ትግል

የሀገራችን የፖለቲካ ሃቅ የሚያስመዘግበን፣ ህዝባችን ሆነ ሀገራችን፣ ትልቅ መቀመቅ ውስጥ እንደ አለን ነው። ይህም የጥቂት ግለሰቦች፣ የጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ወይንም የአንድ ትውልድ ችግር ብቻ ሣይሆን የአሁንና የተከታታይ ትውልድም ነው። ለዚህ አዘቅት መግባት በዋናነት ተጠያቂው የአሁኑ ገዢ ቡድን ሲሆን፣ በተወሰነ ደረጃ፣ ይህንን ዕድል አመቻችተውለት ለዚህ ያበቁት፣ ከፊቱ የቀደሙት የደርግና የአፄው ዘመን ገዢዎችም ናቸው። እንዳቅሚቲም አሁን ያለውን የገዢ ቡድን እንቃወማለን የምንለው አስተዋፅዖ አለን።

በዕርግጥ ምን ያህሉ ድርሻ ለገዢዎቹ ቡድን፣ ምን ያህሉ ደግሞ ለታጋዩ የሚለውን ማስተናገድ አላስፈላጊ ነው። ያለምንም ጥርጥር በአሁኑ ገዢ ቡድን ድርሻ የተሞላው ገበታ ውስጥ የተቃዋሚው ድርሻ አንዲት ጠብታ ናት። ***"ታዲያ ይኼንን ለምን ከቁጥር አስገባችሁት?"*** ብትሉን፣ ለሁሉም መጀመሪያችን ከቤታችን ነውና፣ በቁጥጥራችን ሥር ያለውን አፅድተን ወደ ደጅ ለመውጣት ነው። በዚህ ***ኮተት ኮተት*** እያደረግን ያለውን ያገራችን የፖለቲካ ቅኝት ስናጤን፣ **"ኅብረት ለትግል፣ ለኅብረት ትግል"** ወደሚለው ርዕስ ያመጣናል። ይህ ነው ***እስከመቼ*** ቁጥር ፪ ሙሉ ትኩረቷ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ሰዓት ያለበትን መታፈን የማያውቅ ስለሌለ፣ ***"ታዲያ"*** ህዝቡ ምን ይላል? በሚለው እንጀምር። ዕለት ተዕለት እየተገፋና ከዚህ ግፍ ለመገላገል ግብግብ ገጥሞ ያለው ወገናችን፣ ***መኖሩን እየኖረ፣ መታገሉን እየታገለ፣*** ቀኑን ምሽት፣ ምሽቱን ሌሊት እያደረገ ያነጋዋል።

ይኼንን ደግሞ ከቀን ወደ ሣምንት፣ ከሣምንት ወደ ወር፣ ከወር ወደ ዓመት፣ ከዓመት ወደ ትውልድ፣ እያሸጋገረ ለዚህ በቅተናል። ገዢዎች ለመሰንበት፣ ህዝቡ ነፃ ለመሆን የሚያደርገው ትንቅንቅ ወደ ድርጅቶች ሚና ያመራናል።

ድርጅቶች ምንድን ናቸው? ሚናቸውስ ምንድን ነው? የሚለውን ለማስተናገድ መሞከር አንባቢን መናቅ ስለሚሆንብን አንሞክረውም። መሠረታዊ አንፀባራቂነታቸውን መመልከቱ ግን መንገድ ስለሚሰጥ እንጎበኘዋለን።

ከላይ እንደጠቀስነው በሀገራችን መደረግ ያለበት ለውጥ፣ እጅግ መሠረታዊና ህብረተሰባዊ ግዝፈት ያለው ነው። የአንድ ትውልድ ብቻ ሣይሆን የተደራራቢና የቀጣይ መጪ ትውልዶችም ችግር ነውና። እናም አንድ የፖለቲካ ድርጅት በፈቃዱና በጉልበቱ ህዝቡን የሚያሠልፍበትና በህዝቡ ጫንቃ ላይ አገዛዙን የሚያነጥፍበት ሥርዓት ከመፍትሄ ጎራ አይዘነቅም። ይኼንን ኅብረተሰባዊ ግዝፈት ያለው ለውጥ ለማምጣት ከሞላ ጎደል የመላ ህዝቡን ተሳትፎ የሚያካትት ግንባር መፈጠሩ ግድ ነው። ይቺ መንደርደር **"ኅብረት ለትግል፣ ለኅብረት ትግል"** ወደምትለዋ የዚች ፅሑፍ ርዕስ ታቀርበናለች። መልካም። ዓላማችንም ይኼው ነው። ሃሳባችንን በመቀጠል፣ ይህን የመላ ህዝቡን ከሞላ ጎደል ሙሉ ተሣትፎ የሚያካትት ግንባር ለመመሥረት ደግሞ፣ መላ የታጋዩን ሠፈር የሚጋብዝ ጥሪ መታወጅ አለበት። ይኼንን ተንተን አድርገን ማየት ይኖርብናል።

የዚህ ግንባር ጥራትና ጥንካሬ፣ ከህዝቡ ዕምነትና ፍላጎት ጋር ባለው የዓላማ አንፀባራቂነት ይመዘናል። ህዝቡ በአሁኑ ሰዓት ከገዢው ቡድን የተለየ አማራጭ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ ኢሕአዴግን የሚተካ ሌላ ፓርቲ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። አይደለምና። ህዝቡ የሚፈልገው፣ ከኢሕአዴግ ውጪ ያሉ ታጋዮች መሠረታዊ በሆነ ቁልፍ ሀገራዊ ነጥቦች ዙሪያ ተሰባስበው፣ አንድ አማራጭ ሆነው እንዲቀርቡለት ነው። የማን የድርጅት አባላት ናቸው ቁጥራቸው የሚበዛ? የማን ነው ቁጥራቸው የሚያንስ? አይደለም የህዝቡ ጥያቄ። ምን ያህል ከኢሕአዴግ ድርጅቱ ይቀርባል? ወይንስ ይርቃል? አይደለም የህዝቡ ጥያቄ። ኢሕአዴግን ከነግብረ አበሮቹ ከምርጫው አስወጥቷቸዋልና! ከአንዱ ድርጅት ሌላውን የመምረጥ ሁኔታ፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ፣ ህዝቡ የመረጥኩት ይወክለኛል ብሎ ተማምኖ፣ ድምፁ እንደሚከበርለት አውቆ፣ በምርጫው ሲሳተፍ ነው። ይኼ ደግሞ የአሁን ጉዳይ አይደለም። የአሁን ጉዳይ የሆነው ከዚያ ለመድረስ "ሀገር አድን" ትብብን ነው። ሁሉ ሰውነቷ በሾህ የተወጋ ዠንጀሮ መጀመሪያ መቀመጫየን ያለችውን

እስከመቼ - በዚህ ምርጫ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ታሪካዊና ሀገራዊ ተልዕኳችንን ለመወጣት በየሳምንቱ የምናወጣው መፅሔት ነው።

የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጎዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

ጥር ፳፫ እስከ ጥር ፳፱ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
January 31 to February 6, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፪
Volume I Number 2

ያስታውሷል። ይህ ትብብር ደግሞ በሩ የህዝቡን የመብቱ ባለቤትነት፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና አንድነት፣ እና የሕግ የበላይነትን መቀበል ብቻ ነው። አሁን በሩ ደርሰናል። የሕግ የበላይነትን የተቀበለ፣ የህዝቡን የመብቱ የበላይነት የተቀበለና፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና አንድነት የተቀበለ፤ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ፤ ለዚህ ትብብር ጠሪ አያስፈልገውም። ተጋዥም አይደለም። ባለቤት ነውና። መልካም። እስኪ እንቀጥል። ህዝቡ ኅብረትን ይፈልጋል። አብዛኛው ድርጅት ኅብረትን ከመፈለግ አልፎ፤ የኅብረት ጥሪ ግራና ቀኝ ለፍፏል። ያለኅብረት ማቸነፍ እንደማይቻል አብዛኛው ክፍል ተረድቶታል። ለትግሉ መሣካት ኅብረት ወሳኝ ሆኖ፤ ኅብረቱን ለመፍጠርም ትግል የማይቀር ነው። **እኛ ያለንበት ሁኔታ የሚያሳየው፤ ደግሞ ይኼንን ኅብረት ለመፍጠር ከያዝነው ትግል ጋር ተቆላልፈንና ተወሽቀን መቅረታችንን ነው።** እስኪ እያንዳንዳችን እራሳችንን እንጠይቅ! ለመተባበር ከተጀመረ ስንት ጊዜ ሆነ? ያለኅብረት የሚፈጠረው የሚቀጥለው የሥልጣን ሽግግር፤ የጉልቻ መቀያየር ነው። ይኼንን ሃቅ አልቀበልም የሚል ካለ ከእንቅልፉ እንዲነቃ ፊቱ ላይ ቀዝቃዛ ወሃ መርጨት ነው። በጄ፤ ታዲያ ይኼንን ኅብረት እንዳይፈጠር እንቅፋት የሆኑት ምንድን ናቸው?

የመጀመሪያውና ትልቁ ዕንቅፋት **“የኅብረቱ ባለቤት እኔ ነኝ”** ባይነቱ ነው። ይህ እንግዲህ፣ **“እኔ በጠራሁት ተሠብሠቡልኝ እንጂ እናንተ በምትጠሩት አልመጣም”** ባይነትን ያዝላል። ቀጥሎም፣ **“እኔ የሚገባውንና የማይገባውን እወስናለሁ”** ይከተላል። ከተሻለም፣ **“እሺ እንሰብሰብ። ለኅብረቱ አባልነት መለኪያ ሚዛኑን የማወጣው እኔ ነኝ”** ይታከልበታል። **“ኅብረቱ ቢፈጠርም፤ የኔ ግብ፤ ኅብረቱ የተፈጠረበትን ዓላማ ለማሟላት ሣይሆን፤ ኅብረቱ የኔን ዓላማ ማሟያ መሣሪያዬ አደርገዋለሁ። የኔ ዓላማ ነውና ትክክሉ። ሌሎች የኔ ተከታይ መሆን አለባቸው።”** የሚልም እብሪት አለ። እንግዲህ *በአንድ መልኩ፤* ኅብረቱን የልዩ ቡድኖች ወይንም የራስ ብቻ ክበብ አድርጎ የማስቀመጥ ጉዳይ ነው። ህዝቡ ይኼንን እያለ አይደለም ያለው። ህዝቡ ይኼንን ካላለ፤ ይኼንን ባይ የህዝብ ወገን አይደለም። መልካም። ወደ ኅብረቱ እንመለስ።

ኅብረቱ ባንድ ቀን እህሉ ተሸምቶ፣ ባንድ ቀን ተፈጭቶ፣ ባንድ ቀን ተቦክቶ፣ ባንድ ቀን የሚጋገር እንጀራ አይደለም። የሚፈለገው ኅብረት፤ ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ነጥቦች ዙርያ፤ ማለትም፤ የህዝቡን የመብቱ ባለቤትነት፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና አንድነት፣ እና የሕግን የበላይነት ተቀብለው የሚሰባሰቡ ድርጅቶች ጀምረውት በሂደት የሚያድግ ክንውን ነው። በውጭ ሀገር በምንኖር ኢትዮጵያዊያን መካከል፤ የዚህን ኅብረት መፈጠር የምንወድ ብዙ ግለሰቦችና በድርጅት ውስጥ የተካተቱ ታጋዮች አለን። __እስከመቼ__ ያለውን ሃቅ የምትቀበል የናንተው መፅሔት ናት። በዚህ አጣዳፊ ሰዓት ከዜሮ እንጀምርና ይኼንን ኅብረት እንመሥርት ብላ አትሰብክም።

ይህን ትግል የግሉ አድርጎ ብቻውን የሚሸከመው የለም። ሀገሪቱም የሁላችን፤ ትግሉም የጋራችን ነው። ፊትና ኋላ ሳንል በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን፤ ከህዝቡ ጎን ለመሰለፍ ጠሪያችን ታሪካዊ ኃላፊነታችን ብቻ ነው። ባሁኑ ሰዓት ለመተባበር የተዘጋጁ ግለሰቦች፣ የድርጅት አባል ታጋዮች፣ የድረ ገፅ አዘጋጆችና አጠቃላይ ሀገር ወዳድ ወገኖቻችን እኛም አለን ብለውናል። ቃል በገቡልን መሠረት፤ እኛም ይኼንን ሰፋ አድርገን፤ በመሯሯጥ ላይ ያሉትን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች እየመረመርን ነው። የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን እያጠናን ነው። የእስካሁን ታሪካቸውን እየተመለከትን ነው። በአሁኑ ሰዓት ያላቸውን የሀገሪቱ የአሁን የፖለቲካ አቋማቸውና መፍትሄ ብለው ያመኑበትንና ያቀረቡትን እየተከታተልን ነው። በሚቀጥለው የእስከመቼ ቁጥር ፫ የደረስንበትን እናሳውቃችኋለን። ለዚህ ይረዳችኋል የምትሉት ካለ፤ ብትጠቁሙልን ወይንም በ eske.meche@yahoo.com ብትልኩልን፤ በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

## ውድ ኢትዮጵያዊያን፤

በውጭ ሀገር ነዋሪነታችን፤ በየዕለቱ ወገናችንንና ሀገራችንን በናፍቆትና በፍቅር አንግበን እንወዘወዛለን።

ኢትዮጵያዊነታችን ማንም የማይሠጠን፣ ማንም የማይነፍገን፣ ማንምም የማያዝበት የህልውናችን መሠረት ነው።

አብዛኛዎቻችን ወጣቶች በመሆናችን፤ በዕድሜ ከገፋት ተምረን፣ ታላላቆችን አክብረን፣ ታሪክ የጣለልንን አደራ በአኩሪ ተግባር እንወጣለን።

በታሪክ ተማሪነታችን የህዝባችንንና የሀገራችንን ማንነትና ምንነት ጠንቅቀን አጥንተን፤ ማንና ከየት መሆናችንን በመረዳት እንኮራበታለን።

በአሁኑ ሰዓት ይጠበቅብናል የምንለውን አስተዋፅዖ ለማበርከት ከህዝብ ወግነን የህዝቡን ትግል ለማገዝ ይኼንን ዕርምጃ ወስደናል። ይኼ በሩን ከፍቶላችሁ ለመተባበር እጃችሁን ብትዘረጉ፤ ኢትዮጵያዊ እጅ በናፍቆት ይጠብቃችኋል።